# County of San Diego

ኒክ ማቺዮን ፈች/NICK MACCHIONE, FACHE
የኤጀንሲ ዳይሬክተር

የጤናና ሰብአዊ አገልግሎቶች ኤጀንሲ
የማህበረሰብ ጤና አገልግሎቶች
3851 ROSECRANS STREET, MAIL STOP P-578
SAN DIEGO, CA 92110-3134
(619) 531-5800 • FAX (619) 542-4186

ዊልማ ጄ. ዉተን/ WILMA J. WOOTEN, M.D.
የማህበረሰብ ጤና ኦፊሰር

## የጤና ኦፊሰር ትዕዛዝ

### (የሁሉም በ COVID-19 የተያዙ ወይም መያዛቸውን የጠረጠሩ ሰዎች እራሳቸውን ማግለል)

የኮሮና ቫይረስ በሽታ 2019 (COVID-19) ስርጭት በማህበረሰብ ጤና ላይ ከፍተኛ ስጋትን ፈጥሯል። የሳን ዲዬጎ ካውንቲ በአሁኑ ወቅት በCOVID-19 ወረርሽኝ ምክንያት የታወጀው የጤና አስቸኳይ ጊዜ እና የታወጀው የአካባቢ የአስቸኳይ ጊዜ ተፈጻሚ የተደረገበት ሲሆን የካሊፎርንያ ግዛት ገዥ የአስቸኳይ ጊዜ አውጀዋል። እያንዳንዱ ሰው በCOVID-19 የመታመም ስጋት ያ ለበት ቢሆንም አንዳንድ ሰዎች በእድሜ መግፋት ምክንያት በሚያጋጥማቸው ከባድ ህመም ወይም ስር የሰደዱ የጤና ሁኔታዎች የተነሳ ከሌሎች ሰዎች የበለጠ ለበሽታው ተጋላጭ ይሆናሉ። የCOVID-19 ስርጭትን ለመቀነስ እና የሳንዲዬጎ ካውንቲን የጤና እንክብካቤ ስርአት ከመዳኪም ለመከላከል ለሳን ዲዬጎ ካውንቲ የጤና መኮንን (የጤና መኮንን) በCOVID-19 ተይዘው ህክምና የወሰዱ ወይም በበሽታው መያዛቸውን የጠረጠሩ ሰዎችን እራሳቸውን እንዲያገሉ መጠየቅ አስፈላጊ ሆኖበታል።

በመሆኑም የጤነና መኮንኑ በካሊፎርኒያ የጤናና ደህንነት ደንብ ክፍሎች 101040, 120130, 120175, 120215, 120220, እና 120225 መሰረት የሚከተሉትን ትዕዛዞች አውጥቷል:

1. **ሁሉም በCOVID-19 ተይዘው ህክምና የወሰዱ ወይም በበሽታው መያዛቸውን የጠረጡሩ ሰዎች ወዲያውኑ የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው:**
   a. በመኖሪያ ቤታቸው ወይም ሌላ የመኖሪያ ቦታ እራሳቸውን ማግለል። እራሳቸውን የሚገሉት በጋራ መኖሪያ ቦታ፣ ሆቴል ወይም ብዙ የመኖሪያ ክፍሎች ባሉት መኖሪያ ቦታ ከሆነ እዛ ቦታ ላይ ወደ የትኛውም ሌሎች ክፍሎች አለመግባት። እራሳቸውን ያገለሉ ሰዎች እራሳቸውን ካገለሉበት ቦታ መውጣት ያለባቸው አስፈላጊውን የህክምና እንክብካቤ ለማግኘት ብቻ መሆን አለበት።

   b. ሁሉንም የጤና መኮንን እና የህክምና አቅራቢ መስፈርቶች በጥንቃቄ መመርመር እና በጥብቅ መከተል አለባቸው። (በመኖሪያ ቤት እራስን የማግለል መመሪያዎችን ቅጂ ከካውንቲው የCOVID-19 ድረገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል: https://www.sandiegocounty.gov/content/dam/sdc/hhsa/programs/phs/Epidemiology/COVID%20Home%20Isolation%20Instructions%20for%20COVID-19.pdf)።

   c. ለሁሉም ከነርሱ ጋር የቅርብ ንክኪ ላደረጉ ሰዎች በማህበረሰብ ጤና ኦፊሰሩ የኳራንታይን ትዕዛዝ ላይ በሌላ መልኩ ካልተገለጸ በስተቀር እራሳቸውን ለመጨረሻ ጊዜ ንክኪ ካደረጉበት ቀን ጀምሮ ለ 10 ቀናት ኳራንታይን እንዲያደርጉ ማሳወቅ አለባቸው።

      i. የማህበረሰብ ጤና ኦፊሰሩን የኳራንታይን ትዕዛዝ ከካውንቲው የCOVID-19 ድረገጽ:
         - https://www.sandiegocounty.gov/content/sdc/hhsa/programs/phs/community_epidemiology/dc/2019-nCoV/health-order.html።

ii. አንድ ግለሰብ በCOVID-19 ተይዞ ከተጠረጠረ ወይም እንደተያዘ ከተጠረጠረ ሰው ጋር የቅርብ ንክኪ እንዳደረገ የሚቆጠረው በበሽታው የተያዘው ሰው ምልክቶቹን ማየት ከመጀመሩ በፊት ካሉት 48 ሰአቶች (ወይም ምልክቶቹ የታዩበት ታካሚ ከሆነ የምርመራ ናሙና ከመወሰዱ ከ2 ቀናት በፊት) ጀምሮ ለግለሰቡ ተጨማሪ እራሱን ማግለል አስፈላጊ እስከማይሆንበት ጊዜ ድረስ ይህ ሰው:

- በCOVID-19 ከተያዘው ሰው ወይም እንደተያዘ ከተጠረጠረው ሰው ጋር በ6 ጫማ ርቀት ውስጥ በጠቅላላው ለ15 ደቂቃዎች ወይም ከ24 ሰዐት ለበለጠ ጊዜ ከተገናኘ፣ ወይም
- COVID-19 ከተያዘው ሰው ወይም እንደተያዘ ከተጠረጠረው ሰው የሰውነት ፈሳሾች እና/ወይም አከታዎች (ሳልን ወይም ማስነጠስን፣ የመመገቢያ እቃዎችን በጋራ መጠቀም ወይም ከተመሳሳይ ማስቀመጫ መጠጣትን ጨምሮ በነዚህ ላይ ብቻ ሳይወሰን) መከላከያ በሌለበት መልኩ ከተነካካ ነው።

d. የህክምና እንክብካቤ ሙያተኞችን፣ ይህን ትእዛዝ የሚያስፈጽም የህግ አስፈጻሚ ኦፊሰርን፣ የጤና መኮንን ተወካይን፣ የትኛውንም ሌላ በጤና መኮንኑ የተፈቀደለትን ሰው ወይም ተንከባካቢ ሳይጨምር ከየትኛውም ሰው ጋር በ6 ጫማ ርቀት ክልል ውስጥ አለመገናኘት።

2. **ግለሰቦች በCOVID-19 በመያዛቸው ወይም እንደተያዙ በመጠርጠራቸው ምክንያት እራሳቸውን የማግለል ግዴታ አለባቸው። አንድ ሰው ከሚከተሉት መስፈርቶች መካከል አንዱን ወይም ከዚያ በላዩን የሚያሟላ ከሆነ ወዲያውኑ እራሱን እንዲያገል ይጠየቃል፡**

a. የተረጋገጠ የCOVID-19 ፖዘቲቭ የህክምና ላብራቶሪ ምርመራ ውጤት ከተገኘበት፤ ወይም

b. ከCOVID-19 ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ምልክቶች ከታዩበት (ሳል፣ ትንፋሽ ማጠር ወይም ለመተንፈስ መቸገር፣ ድካም፣ ትኩሳት ወይም ብርድ ብርድ ማለት፣ የጡንቻ ወይም የሰውነት ህመም፣ ራስ ምታት፣ የጉሮሮ መሰርሰር፣ ጣዕም ማጣት ወይም ማሽተት አለመቻል፣ የአፍንጫ ፈሳሽ መብዛት፣ ማቅለሽለሽ ወይም ማስመለስ ወይም ተቅማጥ)፤ ወይም

c. በCOVID-19A መያዙ የተጠረጠረውን ሰው በተመለከተ ይህ ለሀኪም ይገለጻል።

እነዚህ ሰዎች በCOVID-19 የተያዘ ወይም እንደተያዘ የሚጠረጠር ሰው ቫይረሱን በቀላሉ ወደ ሌሎች ሰዎች ሊያስተላልፍ የሚችል በመሆኑ ምክንያት እራሳቸውን ማግለል ይጠበቅባቸዋል። እራስን ማግለሉ የCOVID-19 ስርጭትን ለመከላከል እነዚህን ሰዎች እራሳቸውን ከሌሎች ሰዎች እንዲያገሉ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ እንደ በእድሜ የገፉ አዋቂ ሰዎች እና ስር የሰደዱ የጤና ሁኔታዎች ያሉባቸው ሰዎች የመሳሰሉ ከፍተኛ ስጋት ያለባቸው ሰዎችን እንዲጠበቁ ያደርጋል።

እራሱን ያገለለው ሰው እራሱን ባገለለበት ጊዜ ውስጥ ለየትኛውም ሀኪም ወይም በጤና መኮንኑ ለሚፈቀድላቸው ሰዎች የህክምና ምልከታ እንዲያከናውኑ መተባበር አለበት።

3. **በዚህ ትዕዛዝ ስር የታዘዘው እራስን ማግለል እንደ ተግባራዊነቱ ከሚከተሉት መካከል አንዱ እስከሚከሰት ድረስ መቀጠል አለበት፡**

a. ምልክቶቹ የሚታዩበት ከመጠነኛ* እስከ ከፍተኛ * ህመም የሚታመም ሆኖም የበሽታ መከላከል አቅሙ በከፍተኛ ደረጃ ያልተዳከመ ሰው:

i. ምልክቶቹ ለመጀመሪያ ጊዜ ከታዩበት ጀምሮ ቢያንስ 10 ቀናት እስከሚያልፉ እና

ii. ለመጨረሻ ጊዜ ትኩሳት ካጋጠመው ጀምሮ ቢያንስ 24 ሰአቶች (ያለ ምንም ትኩሳትን የሚቀንሱ መድሀኒቶች) እስኪያልፉ ድረስ እና

iii. ሌሎች ምልክቶቹ መሻሻል እስከሚያሳዩ

b. ምልክቶቹ የሚታዩበት ከከፍተኛ* እስከ እጅግ ከባድ* ህመም የሚታመም የበሽታ መከላከል አቅሙ በከፍተኛ ደረጃ የተዳከመ ሰው *:
   i. ምልክቶቹ ለመጀመሪያ ጊዜ ከታዩበት ጀምሮ ቢያንስ ከ 10 ቀናት እስከ 20 ቀናት እስከሚያልፉ ድረስ እና
   ii. ለመጨረሻ ጊዜ ትኩሳት ካጋጠመው ጀምሮ ቢያንስ 24 ሰአቶች (ያለ ምንም ትኩሳትን የሚቀንሱ መድሀኒቶች) እስኪያልፉ ድረስ እና
   iii. ምልክቶቹ (ምሳ፡ ሳልና የትንፋሽ ማጠር) መሻሻል እስከሚታይባቸው ድረስ
   iv. ከግለሰቡ የህክምና አቅራቢ ወይም የኢንፌክሽን ቁጥጥር ኤክስፐርቶች ጋር የሚደረግ ምክክር ታሳቢ መደረግ አለበት።

c. ምልክቶቹ የሚታዩበት ሆኖን የበሽታ መከላከል አቅሙ በከፍተኛ ደረጃ ያልተዳከመ ሰው *:
   i. በበሽታው ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ ምንም አይነት ምልክቶቹ የማይታዩበት ሰው የመጀመሪያው የCOVID-19 ምርመራ ውጤቱ ፖዘቲቭ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ 10 ቀናት ካለፉ በኋላ እራሱን ማግለሉን ሊያቋርጥ ይችላል።

d. ምልክቶቹ የሚታዩበት የበሽታ መከላከል አቅሙ በከፍተኛ ደረጃ የተዳከመ ሰው *:
   i. የበሽታ መከላከል አቅሙ በከፍተኛ ደረጃ የተዳከመ በበሽታው ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ ምንም አይነት የበሽታው ምልክቶች የማይታዩበት ሰው የመጀመሪያው የCOVID-19 ምርመራ ውጤቱ ፖዘቲቭ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ ከ 10 ቀናት እስከ 20 ቀናት ካለፉ በኋላ እራሱን ማግለሉን ሊያቋርጥ ይችላል።
   ii. ከግለሰቡ የህክምና አቅራቢ ወይም የኢንፌክሽን ቁጥጥር ኤክስፐርቶች ጋር የሚደረግ ምክክር ታሳቢ መደረግ አለበት።

*መጠነኛ፣ መካከለኛ፣ ከባድ እና እጅግ ከባድ ህመሞች ለሚሉት ቃላት ፍቺዎች እንዲሁም ስለ ህጻናት ታካሚዎች እና የበሽታ መከላከል አቅቸው በእጅጉ ስለተዳከመ ግልሰቦች የተመለከተ ልዩ መረጃ ለማግኘት እባክዎ https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/hcp/disposition-hospitalized-patients.html።

ይህ ጊዜ እስከሚደርስ ድረስ እራሳቸውን ያገለሉ ግለሰቦች አስፈላጊ የህክምና እንክብካቤ ለማግኘት ወይም ምርመራ ለማድረግ ካልሆነ በስተቀር እራሳቸውን ያገለሉበትን ቦታ ለቀው መሄድ ወይም ወደየትኛውም የህዝብ ወይም የግለሰብ መገኛ ቦታዎች መግባት የለባቸውም።

4. ይህን ትእዛዝ መጣስ ወይም አለማክበር እንደ ጥፋት ተቆጥሮ በእስር፣ የገንዘብ ቅጣት ወይም በሁለቱም ያስቀጣል (የካሊፎርንያ የጤናና ደህንነት ደንብ ክፍል 120275 እና 120295)። ይህ ትዕዛዝ ተላላፊ፣ በካይ ወይም ተዛማች በሽታን ለመከላከል አላማ በየትኛውም የህግ አስፈጻሚ ኦፊሰር በወሰነ ክልሉ ውስጥ ተፈጻሚ ሊደረግ ይችላል (የካሊፎርንያ አስተዳደር ደንብ ክፍል 26602 እና 41601፣ እና የካሊፎርንያ የጤናና ደህንነት ደንብ ክፍል 101029)።

**ትዕዛዙ ተሰጥቷል።**

Wilma J. Wooten, M.D.

ዊልማ ጄ. ዉተን/ Wilma J. Wooten, M.D., M.P.H.
የማህበረሰብ ጤና መኮንን
የሳን ዲዬጎ ካውንቲ

ቀን: ታሕሳስ 24, 2020 ዓ.ም